# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 49

ጥር 14 ቀን 2015ዓም(22-01-2023)

ባለፈው ሳምንት ባቀረብነው የአገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችን በስፋት የቃኘነው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የገጠመውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ በውስጡ የተፈጠረው ቀውስ በስብሰባ ወጥሮት እንደከረመና በዬስብሰባው ላይም ለእርስ በርስ ፍጥጫና ንትርክ እንደተዳረገ የሚያብራራ ነበር። ከባሕርዳር እስከ ደብረዘይት፣ከዚያም ፣እስከ ደብረብርሃንና ደሴ፣ድረስ የተደረጉት ስብሰባዎች የሥርዓቱን እቶ ፈንቶ ይበልጥ አጋለጠው እንጂ ለገጠመው ቀውስ መፍትሔ አላመጣለትም።የሥርዓቱ ተካፋዮችና አረጥራጮች እንዲሁ በአፋር ከተማም ያደረጉት ስብሰባ ሌላ ማምለጫ ዘዴ ለመሻት የተደረገ እንጂ ለገጠመው ቀውስ መፍትሔ አላመጣለትም።የስብሰባው ጋጋታ ያላሶገደውን ችግር በባለሥልጣኖች ሹም ሽርና የቦታ መቀያዬር ለማድበስበስ ሙከራ የተደረገበት የዚህ ሳምንት ድራማም እንዳለፉት ድራማዎች ሁሉ የመፍትሔ ውጤት ሊያመጡለት እንደማይችሉ ብቻ ሳይሆን ይበልጥ የእርስ በርሱን ንትርክና የተደበቁ ሴራዎችን፣ሌብነትና ማጭበርበሮችን የሚያጋልጡ ምስጢሮችን ይዞ የመጣበት አጋጣሚ ሆኗል።

በሙስናና ሌብነት በማስረጃ የሚጠረጠረው ታከለ ኡማ፣ላለው ሥርዓት በሕገመንግሥት ስም መመሪያ የሆነውን የጥፋት ሰነድ በረዳት አዘጋጅነት ጀምሮ የፍትሕ ሚኒስቴር ሆና ከምክትሏ ጋር በፍትሕ ላይ ስትቀልድ የቆዬችው መአዛ አሸናፊና ሰለሞን የተባለው ምክትሏ በራሳቸው ፈቃድ ሥልጣናቸውን ለቀቁ በሚል ድራማ ሌሎች በሥርዓቱ የሚታመኑ ሁለት ሰዎች ተሾመው በፓርላማ ተብዬው ኮመዲያን በሚሰበሰቡበት አዳራሽ እውቅና ተሰጥቷቸዋል።ወጭና ወራጆቹ ከአንድ የብልጽግና ወንዝ በፕሮቴስታንት እምነት የተጠመቁ ፣በአንድ የጎሰኞች አገር አፍራሽ በሆነ የቃል ኪዳን ሰነድ ላይ እጃቸውን ጭነው የማሉና የተገዘቱ ናቸው። እነዚሁ ከካቢኔ አባልነት እራሳቸውን አሶገዱ የተባሉትና ከሌሎቹም ቦታዎች የተነሱ የኦሕድድ አባላት ለሌላ የውጭ ዓለም አቀፍ ድርጅት መመደባቸውንም የታዘብንበት ሰሞን ነው።ከዚህ በፊት ከካቢኔው የተገለሉት የኦነግ ኦሕዴድ አባላት ያሉበትን ስናይ የነዚህም በውጭ አገር ተቋማትና ድርጅቶች መሾማቸው እንግዳ አይሆንብንም።ጠያቂና ወግድ ባይ በሌለበት አገር ሌሎቹም ዘርፈውና ገለው መደበቂያ የሆናቸው የውጭ ተቋማት ናቸው።በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በፈጠሩት ግንኙነትና የጥቅም ትስስር ለተለያዩ ሥራዎች የመቀጠር ዕድል አግኝተዋል።

የሰሞኑ የዳግማዊት ሞገስ በአፍሪካ ድርጅት ስር ላለው የሰላም የንዋይ ቢሮ(Peace Fund) ዋና ሃላፊ ሆና መመደቧ የሙስና ሰንሰለቱን በግልጽ ያሳያል።ይህች ሴት ላለፉት ብዙ ዓመታት በጎሰኞቹ በኢሕአዴግና በኦነጉ ብልጽግና የጭቆና አገዛዝ በአማራው ስም በተለያዩ የሥልጣን ቦታዎች ተቀምጣ የሕዝቡን ሰላምና አንድነት በማደፍረስ ብዙ ወንጀል የሠራች ተጠያቂ ነች።የሴትዮዋ ማንነት ይህ ሆኖ ሳለ፣የሰላም ተግባራት ያከናውናል ተብሎ ለተሰዬመው ተቋም በሃላፊነት መመደቧ ፣ሰላምን ለማስፈን ሳይሆን ባላት የሰላም ማናጋት ተመክሮና ችሎታ ሌላውን የአፍሪካ ሕዝብ ለማበጣበጥ በባጀት መዳቢዎቹ የተሾመች መሆኗ መታወቅ አለበት።ይህ ተቋም ሰላም ከሰፈነ አስፈላጊ ስለማይሆን በውስጡም የተጠቀጠቁት ሹሞችና ሠራተኞች ቦታ ላይኖራቸው ይችላል።ስለሆነም ሰላም በማናጋቱ ተግባር ይሰማሩ እንደሁ እንጂ ሰላምን ለማስፈን ፍላጎትም ምኞትም አይኖራቸውም።የሰላም መናጋቱ ለእነሱ የእንጀራ መብሊያ ሞሰብ ማለት ነው።እንደምሳሌ አንድ ነገር እንጥቀስ።የአገሩን ስም ከመግለጽ ተቆጥበን በያመቱ የጫካ እሳት እዬተነሳ ንብረትና ህይወት በማጥፋቱ ብዙ የእሳት አደጋ ሠራተኞች ለመቅጠር ተገዶ ነበር።በተደረገው ዘመቻና ጥንቃቄ የጫካው እሳት እዬተቀነሰ መጣ።ታዲያ ያንን

ተከትሎ ብዙ ሰዎች ከሥራ ሊባረሩ ሆነ።ያንን ለመከላከል ሠራተኛው የወሰደው እርምጃ ጫካዎችን ተደብቆ ማቃጠል ነበር።በዚያም የተነሳ ከመባረር ዳኑ ይባላል።።በተመሳሳይም የአፍሪካ ሰላምን ማስከበር በሚል ሽፋን የተሾሙት ከዚህ አይነቱ ሰላም ከማደፍረስ ሴራ ሊወጡ እንደማይችሉ ይህ በቂ ምሳሌ ነው።የእሳት አደጋ ሠራተኞቹን ተንኮል የተረዳው አገር ከጊዜ በኂላ ነቅቶ ሥራውን በፈቃደኞች እንዲሠራ በማድረግ እሳቱን ብቻ ሳይሆን ተንኮለኞቹንም ለመቆጣጠር ችሏል።አሁን በብዙ የአውሮፓ አገሮች የእሳት አደጋ ሥራ ላይ በብዛት በፈቃደኝነት የተሰማሩ ናቸው።ያፍሪካ አገራት ሕዝቦችም በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን ጸረ ሰላምና ጸረ አንድነት ተግባር መቆጣጠር አለባቸው እንጂ በውጭ ሃይሎች ለሚዘወር ተቋምና ቅጥረኞች አሳልፎ መስጠትና ተስፋ ማድረግ አይገባቸውም። የዳግማዊት ሹመት ከጀንያው ወደ ጎተራው ገብታ የምትመዘብርበትን ዕድል የከፈተ ነው።ከኢትዮጵያ ብር ክፍያ ተላቃ ተቀማጭነቷ አዲስ አበባ የሆነ የዶላር ተከፋይ አድርጓታል።ለጥቁር ገበያም ግብአት ሆናለች።ሌላው በፖሊስ አዛዥነት የንጹሃንን ህይወት ያጠፋውና ብዙዎችን ያሰቃዬው የኦነግ አህዴዱ ወርቅነህ ገበዬሁ የተባለ ወንጀለኛም በአንዱ የአፍሪካ ተቋም ውስጥ ገብቶ ዶላሩን እዬሸለቀጠ ነው። ኤጋድ በተባለ ተቋሙም ስም የሚገኘውን ባጀትና እርዳታ ከተባባሪዎቹ ጋር እዬዘረፈ ነው።ለማ መገርሳ የተባለውም የኦነግ ካድሬ እንዲሁ ሕዝብ ሲያበጣብጥ ከርሞ ከፖለቲካው የተገለለ መስሎ የተደበቀበው የዓለም የምግብ ድርጅት(WFO) በተባለው በነጮቹ ዋሻ ነው።በስከጀርባ ግን የኦነግን አገር የማፍረስ ሥራ እያካሄደ ይገኛል።በዚህ ድርጅት መግባቱም እንደ ወያኔው ቴዎድሮስ አድሃኖም ከውጭጭ ሃይሎች ጋር በቅርበት የማደሙን ሥራ አጠናክሮለታል።ሁለቱም የተመደቡባቸው ተቋማት ለሃያላኑ ምዕራባውያን የፖለቲካ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው።ለሃያላኑ ያልገበረ መንግሥትና ሕዝብ በርሃብ ድብን ይበል፣በበሽታ ጥርግርግ ብሎ ይለቅ እንጂ አንዲት ጣሳ እህል ወይም አንዲት ክኒና አያገኝም።

ስለ ታከለ ኡማም የተሰማው ነገር ለይምሰልም ሆነ ከአብይ ጋር ባለው ተግዳሮት ከሥልጣኑ ወረደ ከተባለ በኂላ ስለወሎው የወረኢሉ አውራጃ ከ2 ቢሊዮን በርሚል በላይ የነዳጅ ድፍድፍ መኖር መናገሩ ተሰምቷል። በነገራችን ላይ ወረ-ኢሉ የሚለው ስም ኢሉ የወረረው ቦታ ወረራ ኢሉ ለማለት እንደሆነ ለማሳወቅ እንወዳለን።ወረባቦም የሚለው እንዲሁ ባቦ የሚባለው ኦሮሞ የመራው መንጋ ወሮ የያዘው ለማለት ነው።ወረሂመኖም እንደዚያው። ስያሜዎቹ ወረራውን በመሩት ስም ሲሆን ታሪኩ ከኦሮሞ ወረራ ጋር የተያያዘ መሆኑን ልብ ይሏል።አሁንም ወሎ በጠቅላላው የኦሮሞ ይዞታ ነው የሚባለው ይህንን የወረራ ታሪክ ወደ ጎን አድርጎና ከዶ ፣በተጨማሪም የነዳጁንና የሌላውንም በከርሰ ምድር ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት ቀድሞ ለመንጠቅ በማሰብ ነው።ይህ ግን የሕልም እንጀራ ሆኖ ይቀራል እንጂ በገሃድ የሚሳካ አይሆንም። በወረኢሉ፣በካቤ ውስጥ ለብቻው ተንጠልጥሎ የሚገኝ የጋሎች ሰፈር የሚባል ትንሽ መንደር እንዳለም ማወቁ ለታሪኩ ማስረጃ ይሆናል።የቦታው መጠሪያ ቢኖርም ነዋሪው ማህበረሰብ ግን ተዋልዶና ተቀላቅሎ የወሎ አማራ ሆኗል።

በተከታታይም ከ14 በላይ የሚሆኑ የሥርዓቱ አገልጋዮች በአብይ አህመድ ምርጫ ፕሬዚዴንት ተብላ በተወዘፈችው የሥርዓቱ ወኪል በኩል በፓርላማው ፊት ቀርበው የሙሉ አምባሳደርነትና የአምባሳደርነት ሹመት ሥርዓቱን ለማገልገል በሚያምኑበት የጥፋት ሰነድ ላይ እጃቸውን ጭነው መሃላ ፈጽመው ጸድቆላቸዋል።በዚህ ድራማም ላይ ከሃያ ዓመት በላይ የሥርዓቱ ታማኝ አሽከር የሆነው የብአዴኑ ደመቀ መኮንን መንግሥታችን በሠራው ድንቅ ሥራና አልበገሬነት በዲፕሎማሲው ዘርፍ ተጥሎበት የነበረውን ጫና አሸንፎ ከዚህ ደረጃ ላይ በመድረሱ ተሰሚነታችን ከፍ ሊል ችሏል፤ የተሾሙትም ሹማምንት ይህንን ፈለግ ተከትለው ያጠናክሩታል ሲል ተደምጧል።ይህ የኦነግ አሽከር ለመካድና ሕዝቡን ለማጭበርበር የሞከረው የውጪ ሃይሎች በተለይም አሜሪካና አውሮፓውያን ያስቀመጡበትን ግዳጅ ተቀብሎ መንበርከኩን ነው።ከነዚያም ማሳያዎቹ በዋናነት ወያኔን በሰራው

ከፍተኛ ያገር ክህደትና በፈጸመው የንጹሃን እልቂትና የሃገር ሃብት ዘረፋና ውድመት  በሕግ ሳይጠዬቅ፣ በዱሮ ቦታው ላይ ተመልሶ የሥርዓቱ አካል እንዲሆን መፍቀዱ ፣በተጨማሪም ገሎና አፈናቅሎ በሃይል ነጥቆ ይዞ የነበረውንና ከሁለት ዓመት ወዲህ በባለንብረቱ የአማራው ሕዝብ የተመለሰውን  የወልቃትና የራያን ለም መሬት  በሕገ መንግሥቱ መሠረት በሚል ጫጫታ መልሶ ለማስረከብ የሚያደርገው ጥረት ለማጎብደዱ ማሳያዎች ናቸው።

ከዕሮብ እለት ጀምሮ የተካሂያደው ዓመታዊው የጥምቀት በዓል በደመቀ ሁኔታ በሁሉም ያገራችን መሬት ተከብሮ ውሏል።በጥቂት አካባቢዎች ችግር ቢኖርም ከሌላው ጊዜ በበለጠ የሕዝብ ብዛትና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ደምቆና ተውቦ የታዬበት በዓል ነው።ይህ በሕዝቡ ጠንካራ አልበገሬነት የተገኘ ድል እንጂ በሥርዓቱ መልካም ፈቃድና ችሮታ የተገኘ አይደለም።ለሰንደቅ ዓላማዋና ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መጥፋት ሽንጡን ገትሮ የሚታገል ሥርዓት ካቅሙ በላይ ሆኖበት እንጂ እንደፍላጎቱማ ቢሆን ኖሮ ከምድረገጽ ለማጥፋት  አይመለስም ነበር። ላለፉት አራት ዓመታት ቤተ እምነቶችን ሲያቃጥል፣ምዕመናኑን ሲያርድና ሲያሳርድ የኖረ ሥርዓት ከዚያ እኩይ ተግባሩ ይታቀባል ማለት ዘበት ነው።መጠበቅም ጅልነት ነው።

በዓሉ በተጀመረበት ቀን ፌዴራል ፖሊስ ተብዬው ጸረ ሕዝብና የጥፋት ሃይል  በሕዝቡ ገንዘብ ከቱርክና ከሩስያ የገዛቸውን ሜካናይዝድ የጦር መሣሪያዎቹን ይዞ አደባባይ በመውጣት የፍርሃት ድባብ ለማስፈን ሞክሮ ነበር።ይህ ጠብ ያለሽ በዳቦ ላላስፈላጊ ብጥብጥ ግብዣ ቢሆንም ሕዝቡ ንቆ አልፎታል፤የጥምቀት በዓሉንም በፈለገው መልክ አክብሯል።ይህንን የሕዝበ ክርስቲያን በዓል የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ የጎሰኞቹ ስብስብ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጓል።ከነዚያም ውስጥ በኢሚራት ከተማ በአቡ ዳቢ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለብዙ ዓመታት ባደረገችው ጥረት ካገሩ መንግሥት ጋር የተደረሰን ስምምነት አብይ አህመድ  በሱ ጥረት የተገኘ ለማስመሰል ያደረገው ድፍረት ነው።የአገሪቱ መንግሥት ለባለቤቱ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ማስረከብ ሲገባው ለጥቅም አጋሩ ለአብይ አህመድ የፖለቲካ ሽቀጥ ማራገፊያ እንዲሆን በዚህ መልኩ ማሳወቁ ትክክልና ተገቢ አይደለም።አብይ አህመድ ወደ አቡዳቢ የሄደበት ምክንያት ይህንን ለመረከብና ለማብሰር ሳይሆን የንግድ ሰንሰለቱን ለማጥበቅ ሲል ነው።የኤኮኖሚ ሚኒስትር ተብዬውን አህመድ ሽዴን አስከትሎ  ከአገሪቱ መንግሥት ጋር ያደረገው ውልና ስምምነት ምን እንደሆነ ዝርዝሩ ባይታወቅም የመሸጥና የመለወጥ ውል እንደሆነ ግን ለመገመት አያቅትም። ለይምሰል ከወጡት ውሎች ውስጥ አንዱ በሁለቱ አገሮች መካከል የሃይል ማመንጫን በተመለከተ በጸሃይ ጨረር ከ500 ሜጋ ዋት በላይ የሃይል ማመንጫ ውል እንደተፈረመ የተገለጸው ነው።ለዚያ ኢትዮጵያ የምትከፍለው ምን እንደሆነ ግን የሚታወቅ የለም።ያላት ለም መሬትና ማዕድን ስለሆነ ከዚያ ሌላ የምትሰጠው እንደማይኖር ይታወቃል። ከዚህ ከኤኮኖሚው ጀርባ የኢሚራት እንቅስቃሴና ዓላማ እንደሌሎቹ አገራት  የራሷን ፍላጎትና ጥቅም ለማስከበር ስለሆነ ሁሉንም አማራጭ የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ጭምር እንደምትጠቀም መዘንጋት የለበትም። በምንም መንገድ ለሰማይ ቤት ጽድቅ ብሎ የሚሠራ የባዕድ አገር የለም።በአገሯም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እንዲገነባ መፍቀዷ በሚያምር የስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ፈንጂ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት አለን።የቤተክርስቲያኑ መሪዎች ከመፈንጠዝ ባለፈ አደጋውን ማዬት ይኖርባቸዋል። “ከባዕድ የጎረሱት በሶ ይወጣል ደም ጎርሶ” የሚለውን ያገራችንን አባባል ሊያጤኑት ይገባል።

አብይ አህመድ በሚመራት አገር ውስጥ የራሱ የፖለቲካ ድርጅት የሆነው ኦነግ ቤተክርስቲያናትን እያቃጠለ፣ምዕመናንን እያረደ ማቆም አቅቶት ከባሕር ማዶ ድረስ ሄዶ የቤተክርስቲያኗን ጥቅምና ክብር ያስከብራል ብሎ መጠበቅ ከሞኝነትም በላይ ጅልነት ነው።ከዚህም ቀደም በኢትዮጵያ የፕሮቴስታንቱን መስፋፋት  50ኛ ዓመት ሲያከብር ያደረገው የዘለፋና የማጣጣል ንግግር መረሳት የለበትም።በዚያን ጊዜ

አምላክ የቅራቅንቦ አምላክ አይደለም ሲል ጽላቱን፣መጽሃፍቱን፣ ጃንጥላውን፣ከበሮውን፣ጽናጽኑን፣ ቃጭሉን፣አልባሳቱንና መቋሚያውን በቅራቅንቦነት መድቧቸዋል።ቤተክርስቲያኗንም ልትውጥ አፏን የከፈተች አምበሳ ግን በጽናታችን የተሸነፈች ሲል ተዛብቶባታል።ታዲያ ለኦርቶዶክስ እምነት ይጨነቃል ተብሎ ይታሰባል?በጭራሽ!

በጃልሜዳው የጥምቀት አከባበር ላይ ንግግር ያደረገው አንዱ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ፣አረንጓዴ ቢጫና ቀዩን ሲያይ የሚያንቀጠቅጠው የኦነጉ ሹመኛ ቀጀላ መርዳሳ ነበር።እሱም የበዓሉን ታሪካዊና መንፈሳዊ እንዲሁም ኢትዮጵያዊነት ይዘቱን በማኮሰስ በዋናነት የቱሪስት ገበያ፣ የኤኮኖሚ ምንጭ አድርጎ የማቅረቡን ድፍረትም ታዝበናል።ከዚህ አገር ጠል ከሆነና ከመሰሎቹ የተለዩ ኢትዮጵያዊነት ተአምር አይጠበቅምና ችላ ብለነዋል።እነዚሁ ጉደኞች ክልላችን ብለው መስመር ዘርግተውና ሰይመው ቦጭቀው በያዙት የአዲስ አበባ ክፍለ-ከተሞች በለሚኮራና በጀሞ የሚኖረው ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ሕዝብ ጥምቀትን በሚፈልገው መንገድ እንዳያከብርና የሚኮራበትንና የሚወደውን ሰንደቅ ዓላማውን እንዳያውለበልብ ከልክለውታል።ባለፈው ዓመት የአምስት ወጣቶች ሕይወት ለማለፉና ለብዙዎች መቁሰል ምክንያት የነበረው የዋይብላ ማርያም የመልስ አከባበር እንደነበረ አይዘነጋም።በዛሬው የጥምቀት አከባበር ላይ ግን ምንም እንኳን ቁሮ የተባለ በእኛ ቀሮ የምንለው ሐላቀር የኦነግ መንጋ በመንግሥት የጸጥታ ሃይሎች ሽፋን ድንጋ፣ በመወርወር ትንኮሳ ባይቀርም በምእመናኑ በተለይም በወጣቱ ትእግስት፣አስተዋይነት ብሎም ቆራጥነት ታቦቷን በደማቁ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በመዝሙርና ዘፈን አጅበው ከመንበሯ አድርሰዋል።

በተመሳሳይም፣ለሚኮራ፣ ቦሌ ቡልቡላ፣ገሞ፣ደብረዘይት፣በተባሉት ቦታዎች እንዲሁ የሥርዓቱ የኦነግ አሸባሪዎች ትንኮሳ በማድረግ በምዕመናኑ ላይ ጥቃት አድርሰዋል።ከነዚያም ውስጥ በቦሌ ቡልቡላ የደረሰው ከፍተኛ ነው።ወጣቶች የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና የአጼ ቴዎድሮስን ምስል ያለበት ቲሸርት በመልበሳቸው የጸጥታ ሃይሎች በከፈቱት ተኩስ ጊዳን ታዬ የተባለው የታክሲ ረዳት ወጣት ህይወቱ ስታልፍ ሌሎቹ አምስት ወጣቶች ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው በሕክምና ላይ እንደሚገኙ ያገኘነው ዜና ያረጋግጣል።የወጣት ጊዳን ታዬ አስከሬን ወደ ትውልድ ቦታው ጎጃም መሄዱንም ሰምተናል።ፈጣሪ ነፍሱን በጻድቃን ቦታ ላይ ያስቀምጣት እንላለን።ጎሰኛና ጸረ ሕዝብ ስርዓት እዬደገፉ በህይወት ከመኖር ይልቅ ለአገርና ለሕዝብ ሲሉ መሞት ህያውነት ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ የዘንድሮው የጥምቀት በዓል ካለፈው ዓመት በጣም የተለዬ ነበር።አማራ ፣ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ጉራጌ፣ጋሞ፣ሲዳማ፣ወላይታ፣ሶማሌ፣ጋምቤላ---ወዘተ ሳይለይ፣በሰሜን፣በደቡብ፣በምሥራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር ሕዝብ ወጥቶ አንድ ላይ ሆኖ ያከበረበት፣የአንድነቱን ልክና መጠን፣ ወርድና ስፋቱን ያሳዬበት ነበር።ሕዝብ ከቆረጠና በአንድ ላይ ከቆመ ያሰበውንና የሚፈልገውን ለማግኘት እንደማይሳነው ይህ ትልቅ ምሳሌ ነው። በዚህ የጥምቀት በዓል ላይ ከታዩት አኩሪና የኢትዮጵያዊነት ያንድነት መንፈስ በሙስሊም እምነት ተከታዮች በኩል የታዬው አብሮነትና አንድነት፣ መከባበርና መተሳሰብ ነው።በድሬ ዳዋ፣በጎንደር፣በጅግጅጋ፣በደሴ፣፣በአዲስ አበባ በመርካቶና ቁራ ለምእመናኑ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት አድርገው ማስተናገዳቸው ለጸረ አንድነት ሃይሎች ተጨማሪ እራስ ምታትና ሽብር የለቀቀባቸው ሆኗል።ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኢትዮጵያ ነች የማለቱ ምስጢር የተገለጠበትና የተረጋገጠበት ይህ የጥምቀት በዓል አከባበር ነው። በዚህ የተበሳጨው የሥርዓቱ ፖሊስ ወጣቶችን እያደነ በዬእስር ቤቱ ማጎሩን አሁንም ተያይዞታል።የቆሰለ ነብር ሆኗል።ግን መፈራገጥ ለመላላጥ ካልሆነ በቀር የሕዝቡን የለውጥ ማዕበል የሚቀለብሰው አይሆንም፤የተከፈለው መስዋእትነት ተከፍሎ የኢትዮጵያ ነጻነትና አንድነት የሕዝቧ ይረጋገጣል።

ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ብሎ ያለውን የክት ልብሱን ለብሶ አምሮና ተውቦ የወጣው ሕዝብ ለነጻነቱና ለአገሩ አንድነት በልቡ አምቆ ያስቀመጠውን ድፍረቱንና ቆራጥነት ፊትለፊት አውጥቶት ቢጠቀምበትና የሰፈነውን የጎሰኞች ሥርዓት ቢታገል ለማሸነፍ የሚችል መሆኑን ይህ የጥምቀቱ በዓል አከባበር ለድሉ ምሳሌ ነው።

ሌላው በዚሁ የሎሚኮራ ውስጥ የዛፍ አደባባይ በ1.3ቢሊዮን ብር ወጭ በስምንት ወራት ውስጥ እሠራለሁ ብላ የኦነግ ኦሕዴዲ ከንቲባ አዳነች አቤቤ መጀመሩን ይፋ አድርጋለች።በዚህም በዚያም ብሎ የስርቆትና የዘረፋ ሰበብ መፍጠር እንጂ የነዋሪው ሕዝብ አጣዳፊ ችግር አደባባይ ሆኖ አይደለም። የመኖሪያ ቤቱን እያፈ,ሱበት፣ተወልዶ አድጎበትና ከሚኖርበት ቦታ እያፈናቀሉ ለሕዝቡ ጥቅም ተሠራ የሚሉት ቀልድ ይዘቱ የሌብነት በር መክፈት ከመሆን ያለፈ አይደለም።

በአማራው ክልል ብአዴን በተባለው የኦነግ አሽከር ፋኖን የማሳደዱ ተግባር እንደቀጠለ ነው።የጥምቀት በዓሉን በሚያከብሩ የፋኖ አባላት ላይ ያፈና ቡድን አሰማርቷል።የወልቃይትና የራያንም መሬት አሳልፎ ለመስጠት በሚያመቸው መንገድ ሁሉ ሙከራ በማድረግ ላይ ነው።ዓይኑን በጨው ያጠበው ደመቀ መኮንን የተባለe የሥርዓቱ ኢጋሰስ የድፍረቱ ድፍረት የአማራውን ወጣት ለመሰብሰብ ጥሪ ማድረጉን ሰምተናል።ይህ ጅላጅል ባለፉት 30 ዓመታት በአማራው ላይ የፈጸመው በደል ሳይረሳ ለዚህ ድፍረቱ በዝምታ መታለፍ አለበት አንልም።በሥልጣን ወንበሩ ዙሪያ የሚያንዣብበውን የመነጠቅ አደጋ ለመከላከል ወይም የመደበቂያ ጉድጓድ ለመቆፈር አስቦ ያደረገው ሙከራ ከመሆን ያለፈ ነው አንልም። ሙከራው ግን ይከሽፋል።በሱና በመሰሎቹ በብአዴን ተብዬው የባንዳ ስብስብ የሚከበር የአማራ ሙብትና ነጻነት አይኖርም።

በአንጻሩ የወያኔ ደጋፊ በሁሉም ከተማ በተለይም በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ታላላቅ ሆቴሎች ውስጥ አስረሽ ምችው ድግስ አዘጋጅቶ ሲጨፍር ሰንብቷል።የምንጠይቀው የትግራይ ወገኖቻችን ለምን ተደሰቱ  ሳይሆን ለምንና በምን ምክንያት ለመጨፈር ተነሳሱ የሚለው ነው።ከ600 ሺህ ሕዝብ በላይ የተጨፈጨፈበት ማህበረሰብ፣ኢትዮጵያዊነቱን ተገፎ በጎሳ አጥር ውስጥ ተከርችሞ የኖረ ሕዝብ፣ ለመከራ ያጋለጡትን፣ በስሙ የነገዱትን ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡልኝ ይላል እንጂ እንደ ድል አድራጊ ከበሮ ይዞ የሚደልቅበት ምክንያት አይታዬንም።አሁንም ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ በተለይም ከአማራው ማህበረሰብ ጋር የነበረውን የጋራ ማንነትና ህብረት አድሶ ለእሱና ለሌላው ኢትዮጵያዊ መከራና ስቃይ፣የእርስ በርስ ግጭት የዳረጉትን የወያኔና የኦነግ ስብስቦች ታግሎ መጣል ይኖርበታል።ያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው እውነተኛ ደስታና ጭፈራ የሚያምረው።የጋራ ደስታና ጭፈራም የሚሆነው።

አብይ አህመድ ሕዝቡን ለማጭበርበርና የዛለ ጉልበቱን እንደገና ለማጠንከር ከሰባ በላይ የሚሆኑትን በተለያዩ ቦታዎች ሲያገለግሉ የነበሩትን አድርባዮች በሌሎች ታማኞቹ መተካቱ ተሰምቷል። ወጣም ወረደም  መሰረታዊ ለውጥ ስለማያመጣ ሕዝቡም ጉልቻ ቢለወጥ ወጥ አያጣፍጥም ብሎ ተርቶባቸዋል።እኛም ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ወይም አሸዋም ሆነ ጠጠር ያው የድንጋይ ዘር! ብለነዋል። በነዚህ በኩል ሊፈጸም የሚፈለገው አንዱና ዋናው ተግባር ያገሪቱን ተቋማትና የሃብት ዘርፎች በነጻ ገበያና በግል ይዞታ ስም  ለባዕዳን መሸጥና መለወጥ የሚያስችል የኤኮኖሚ ፖሊሲ ማጽደቅና ተግባራዊ ማድረግ ነው።የምዕራባውያን በተለይም የአሜሪካኖች ፍላጎት ይህ እንዲሆንላቸው ነው።እነሱ የማይቆጣጠሩት አገርና ተቋም ገደል ቢገባ ደንታቸው አይደለም።እንዲፈራርስም ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ።ከወያኔና ከኦነግ ጋር ያስተሳሰራቸውና በአማራው ላይ እንዲረባረቡ  ያደረጋቸው ይኸው አቋማቸው ነው።

ሥርዓቱ በዘረጋው የውይይትና በብሔራዊ መግባባት ኮሚቴ ስም የተቋቋመው ቡድን ሥርዓቱን በማዳን ለባሰ ስቃይና መከራ የሚዳርግ እንጂ ለችግሩ መፍትሔ አይሆንም።እውነተኛ እርቅና ሰላም በሕዝብ መካከል በሚደረግ መቀራረብና ችግሩን ተወያይቶ በሚፈጠረው መፍትሔ ነው።ለዚያም ሕዝቡ ይወክሉኛል ብሎ የመረጣቸው፣የሕግ ባለሙያዎች፣የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣የሙያ ዘርፍ ተወካዮች፣ወጣቶች፣የሃይማኖት ተቋማት፣በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑና ለአንድነት የቆሙ የዬጎሳው ተወካዮች የሚካተቱበት አገራዊ መልክ ያለው ኮሚቴ ሲመራው ነው። ከዚህ የተሻለ መውጫ መንገድ የለም።የአብይና የመሰሎቹ መንገዶች ሁሉም ወደ ሲኦል የሚወስዱ ናቸው።

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጣጠል!የጎሰኞች ሥርዓት ይደምሰስ!!